# ግዞት፥ ስደት፥ ፍልሰት

## ጌታቸው ኃይሌ

ከላይ በሰጠሁት ርእስ ስር የምጽፈው "ድርሰት" በየቀኑ ከሚነበበው ለየት ያለ ሐሳብ-አዘል የመዝናኛ ንባብ ለሚፈልግ ነው።

የሰው ልጅ አገሩ ምግባሩ፤
እንዳገሩ ይኖሩ፥ እንደ ወንዙ ይሻገሩ፤
ከጠላት ጉረስ፤ ወደወገንህ ተመለስ፤
ከሐዲ ያጎረሰውን እጅ ይነክሳል፤
ዘይሴሰይ እክልየ አንሥአ ሰኰናሁ ላዕሌየ፤
ውሻ በበላበት ይጮሃል።

አገሬ ገብቼ ሰውነቴ ታውቆ፥
እንኳን እህል ውኻ በበላሁ እንቆቆ።

የፍጥረት ሁሉ አገሩ ተፈጥሮ/ተወልዶ ያደገበት ቦታ ነው። ይኸም የሰውን ልጅንም ይጨምራል። አንድ ቦታ ተፈጥሮ አንድ ቦታ ማደግ ከላይ የሚሰጥ እንጂ በምርጫ የሚገኝ አይደለም። ፍጡር ሲያድግ ተፈጥሮ ከአደገበት ጋር በፍቅር መውደቅ ይመጣበታል፤ ምክንያቱም አስተዳደግ ፍጡርንና አካባቢውን ስለሚያፃምር ነው። አዳጊው የአካባቢው አካል ይሆንና አካባቢን መውደድ ራስን መውደድ ይሆናል። ተፈጥሮ ያፃመረውን ማለያየት መብት መጣስ ነው። አንድ ሰው የትውልድ አገሩንና ነዋሪዎቹን ከማንም አገርና ሕዝብ አብልጦ ቢወድ ጥሎሽ ስለሆነ አይፈረድበትም።

**ግዞት፤**

ግዞት፤ አንድ ሰው ባለሥልጣንን የሚያስቀጣ ጥፋት ሲፈጽም፥ ቅጣቱ የሚወደውን ማሳጣት ይሆናል። ወላጆች ከሆኑ ልጃቸውን ለተወሰነ ጊዜ ጨዋታ ይከለክላሉ፤ የንስሐ አባት ከሆነ አጥፊውን የተወሰነ ጊዜ ያስጾመዋል። ግዞትም በመንግሥት ደረጃ መቀጮ ነው፤ ግዞት መቀጮ የሚሆነው የሚያፈቅሩትን አካባቢ ለመንሣት ነው። የግዞት ዘመን ይረዝም ያጥር ይሆናል እንጂ ጊዜያዊ ነው። ዘመኑ እንዳለቀ ተቀጪው ወደ ሀገሩ ይመለሳል። በተጋዘበት ቦታ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ቢወዳጅም በፍቅር ይለያቸዋል እንጅ፥ ከእነሱ ጋር ስለተወዳጀ እዚያው ቀርቶ የዚያ ሀገር ሰው አይሆንም፤ ከሆነም የተለመደ አይደለም።

ግዞት በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም የተለመደ ቅጣት ነበር። የሳቸውን ዘመን የግዞት ቅጣት ለየት የሚያደርገው፥ በሹመት ስምም መፈጸሙ ነው። የማህል ከተማውን ባለሥልጣን የዳራገር ገዢ፥ የመስኮብ አምባሳደር ያደርጉት ነበር።

ስለግዞት በተነገረ ቊጥር በኢትዮጵያ ታሪክ ከሚነገሩት ውስጥ አፄ ዓምደ ጽዮን የአባቱን ዕቅብት በማግባቱ የገሠጹትን መነኮሳት ወደዝዋይና ወደሌሎች ቦታዎች ማጋዙ ሲሆን፥ ከሁሉም የሚያስገርመው አፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘርአ ጽዮን የተባለውን መኰንን የቀጣው የግዞት ቅጣት ነው። የንጉሡ ታሪክ ጸሐፊ እንዲህ ይላል፤

ለዘርአ ጽዮንሰ ዘተሰምየ ዘርአ ሰይጣን በነቢበ ሐሰት ዘአቅተለ ብዙኃነ መነኮሳተ
ወደባትረ ወኰሎ እደ ወአንስተ ሶበ ከሰተ ሎቱ እግዚአብሔር ብዙኃ ዓመፃሁ
አመንኰስዎ ወአግዓዝዎ ውስተ ሐይቅ።

ውሸት በመናገር ብዙ መነኮሳትና ደብተራዎች፥ ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ያስገደለውን፥ ዘርአ ሰይጣን የተባለውን ዘርአ ጽዮንንም፥ ብዙ ክፋቱን እግዚአብሔር ሲገልጥበት አመንዝሮሰው ወደ ሐይቅ አጋዙት።

ደቂቀ እስጢፋኖስ የተባሉ የዚህ ንጉሥ ተቃዋሚዎች በተጋዙበት አገር ሁሉ ደጋፊዎች ማግኘታቸው የግዞቱን ቅጣትነት ዋጋ አሳጥቶት ነበር።

በሃይማኖት ታሪክ በሰፊው የሚነገረው፥ የእስራኤላውያን ግዞት (ፂዋዌ) ነው፤ ናቡከደነጾር የሚባለው የባቢሎን ንጉሥ በ586 ቅድመ ክርስቶስ ኢየሩሳሌምን አፍርሶ ንጉሡንና መኳንንቱን ካህናቱን ወደ ባቢሎን አግዟቸው ነበር። እስራኤላውያን እዚያ በግዞት በነበሩበት ዘመን፥ "ውስተ አፍላገ ባቢሎን ህየ ነበርነ ወበከይነ" (በባቢሎን ወንዞች አጠገብ እዚያ ተቀመጥንና አለቀስን) እያሉ ያዜሙት የነበረውን መዝሙር 136 የኢትዮጵያው ንጉሥ ከመኳንንታቸውና ከካህናታቸው ጋር እንግሊዝ አገር ተሰደው በነበረበት ጊዜ ያዜሙት ነበር፤

> በባቢሎን ወንዞች አጠገብ እዚያ ተቀምጠን ኢትዮጵያን ባስታወስናት ጊዜ አለቀስን፤ . . . ኢትዮጵያ ሆይ፤ አንቺን ብረሳሽ . . . ቀኝ እጄ ይክዳኝ፤ አንቺን ባላስታውስሽና ታላቅ ደስታዬ አድርጌ ባልቈጥርሽ ምላሴ ከትናጋዬ ይጣበቅ። . . . ኢትዮጵያን አፍርሷት፥ አፍርሷት እስከመሠረቷ እያሉ መጮኻቸውን አስታውስ። . . .

እስራኤላውያን በተጋዙ በሰባ ዓመታቸው ተመለሱ፤ የኛዎቹ ከአምስት ዓመት በኋላ እንደተመለሱ እናስታውሳለን። እስራኤላውያን ባቢሎንን ለቀው ለመመለስ ሲዘጋጁ አንዳንድ ቤት ውስጥ ታላቅ ጭንቅ ተፈጥሮ ነበር። የሰባ ዓመት የስደት ኑሮ ከአገሬው ሕዝብ ጋር መጋባትን አስከትሎ ስለነበረ ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ ነቢያቱ የአምላክን ትእዛዝ አስታወቋቸው። እነሱ ግን ሚስቶቻቸውንና ከሀገሬው ሴቶች የወለዷቸውን ልጆቻቸውን ትተን አንሄድም ብለው ይዘዋቸው መጡ። ግን ኢየሩሳሌም መግባት ስላልተፈቀደላቸው ሰማርያ ሰፈሩ።

**ስደትና ፍልሰት፤**

ስደትና ፍልሰት በብዙ ረገድ ይመሳሰላሉ፤ ስደትና ፍልሰት በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ምክንያት የሚወጹትን አገርና ኅብረተ ሰብ ጥሎ ወደሌላ አገር መሄድና በአላደጉበት ኅብረተ ሰብ ማህል መኖር ነው። የቅጣት ትርጉሙ የሚወዱትን ማሳጣት ከሆነ፥ ስደትም እንደ ግዞት ቅጣት ነው። ግን ተፈጥሮ ያፃመረውን ሰውንና አካባቢውን ማለያየት መብት መጣስ ነው። ስደተኞቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደትውልድ ሀገራቸው ካልተመለሱ፥ የስደቱ ሀገር ብዙ ጊዜ የስደተኞቹ፥ አለዚያም የልጆቻቸው የራስ ሀገር ይሆናል። ስደተኞች ጥገኞች ናቸው። ጥገኞች በተሰደዱበት አገር ሁል ጊዜ አይቀናቸውም፤ ይጎሳቆሉና ለመመለስ ይይዘጋጃሉ፤ ሰውዬው፥

> አገሬ ገብቼ ሰውነቴ ታውቆ፥
> እንኳን እህል ውኻ በበላሁ እንቆቆ።

ያለው ስለዚህ ነው። በዓሥራ ሰባተኛው ምእት ዓመት የኢዮብ ሉዶልፍ ግዕዝ አስተማሪ የነበሩት አባ ጎርጎርዮስም ጀርመን አገር በነበሩበት ጊዜ ተመሳሳይ ስሜት ተሰምቷቸው ነበር። ፍልሰት ከስደት የሚለየው ፍልሰት ምክንያቱ ኢኮኖሚ ሲሆን የስደት ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ከጭቆናን ለማምለጥ ነው። ዓለምን ጥሎ ገዳም መግባትም ፍልሰት ይባላል። የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ መነኮሳቱን ፈላሲ/ት፥ ፈላስያን/ያት ይሏቸዋል። ከዘመነ አክሱም ጀምሮ እስከኛ ዘመን ድረስ የተፈጸሙት ውስጣዊ ስደትና ፍልሰት የኢትዮጵያ አንድነት መሠረቶች ናቸው፤ ሰሜኑን ከደቡብ፥ ምሥራቁን ከምዕራብ አስተሳስረውታል።

ስደተኞች ላስጠጓቸውና ለረዷቸው ግን ባለውለታዎች ናቸው:: የሀገራቸው መሪዎች የበደሏቸውንና ያሳደዷቸውን ተቀብለው ከአላቸው ጥሪት ከአካፈሏቸውና የሀገሬው ሰው የሚያገኘውን መብት ሁሉ እኩል ከሰጧቸው ባለውለታዎች መሆናቸው አያከራክርም:: ባለውለታ መሆናቸውንም በልዩ ልዩ መንገድ እንዲገልጹ ጨዋነታቸው ያስገድዳቸዋል:: ለምሳሌ፥ እንደ ፕሮፌሰር ፓንክረስት ኢትዮጵያን አገራቸው አድርገው ልጆቻቸውን አሉላ ማለት ወይም ሌላ ኢትዮጵያዊ ስም መስጠት፥ "በባለውለታዬ አገር ቅበሩኝ፤ ወደትውልድ አገሬ አትመልሱኝ" ማለት ጨዋነት ያስገደደው ታላቅነት ይመስለኛል:: ክቡር ደጃዝማች ዶ/ር ዘውዴ ገብረ ሥላሴ የተቀበሩት በተከበሩበት በአዲስ አበባ ከተማ እንጂ በትውልድ ሀገራቸው በአክሱም አይደለም:: ወላጆች ለልጆቻቸው የሌላ ሀገር ስም የሚሰጡት ያባቶቻቸውን ንቀው የሌላውን ሀገር ባህል አክብረው ከሆነ ወቀሳ ይገባቸዋል፤ ባለውለታ መሆናቸውን፥ "ሀገሩ ሀገሬ ሆኗል" ማለታቸው ከሆነ አድናቆትን ያተርፋሉ እንጂ ወቀሳ የለባቸውም:: እንግሊዛዊው ፓንክረስት ለልጁ የሐበሻ ስም ሲሰጥ ያደነቁ ኢትዮጵያውያን ለልጆቻቸው በተሰደዱበት ሀገር የሚኖሩ ሰዎችን ስም ቢሰጡ የሚያስነቅፋቸው ምክንያት አይታየኝም:: "ልጄን በሀገሬ እንጂ በሀገሬው ሕዝብ ስም ሞኒካ፥ ኤሪካ አላልኩም" ማለት ማስመስገን ብቻ ሳይሆን ማስነቀፍንም ያስከትላል:: እንዲያውም አደገኛ ነው፤ አማራ ያልሆኑ ቤተ ሰቦች አዲስ አበባ ላይ ለወለዷቸው ልጆች የአማራ ስም መስጠታቸው ሊያስነቅፋቸው ነው:: ሊያስነቅፍ የሚችለውስ አዲስ አበባ ላይ የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች በፈረንጅ ስም ሲጠሩ ማየታችን ነው::

ባህላችን ግን በዚህ ጉዳይ ግልጽ የሆነ አቋም አያሳይም:: ለምሳሌ፥ እስራኤላውያን ከግዞት (ከፂዋዌ) ሲመለሱ ከሀገሬው ሕዝብ ያገቧቸውን ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ ነቢያቱ ያዘዙትን ቤተ ክርስቲያናችን የሚደገፍ ሐሳብ መሆኑን ትቀበላለች:: ሌላ ምሳሌ ለመጥቀስ፥ አንድ ጻድቅ የሃይማኖት መምህር ራቅ ብሎ ሄዶ ሃይማኖት ሲያስተምር ከሞተ፥ የትውልድ አገሩ ሰዎችና ያስተማረበት አገር ሰዎች "እኛ ዘንድ ይቀበር፤ እኛ ዘንድ ይቀበር" በማለት በአስከሬኑ ላይ ይጣላሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ "የሰው ልጅ አገሩ ምግባሩ"፤ "እንዳገሩ ይኖሩ፥ እንደ ወንዙ ይሻገሩ" የሚል አስተሳሰብ ያስይዘንና፤ ወዲያው "ውሻ በበላበት ይጮሃል" የሚል አነጋገር ያመጣል:: አነጋገሩ ነቀፌታ ከሆነ ታማኝነትን መንቀፍ ይሆናል:: ውሻ ለታማኝነት በአርአያነት የሚጠራ ወዳጅ ነው:: ስለዚህ በአነጋገሩ ውስጥ ነቀፌታ ካለበት ነቀፌታው የውሻን ታማኝነት ሳይሆን የሰውን እምነት አጉዳይነት ነው:: ምሳሌው የተተረከው፥ በአንድ በኩል የውሻ ታማኝነት ለማድነቅ፥ በሌላ በኩል የሰው ልጅ እምነት አጉዳይነትን ለመንቀፍ ከሆነ፥ የ"ውሻ በበላበት ይጮሃል" ምሳሌ አንድምታ፥ "ውሻ እንኳን ከሰው ተሽሎ በበላበት ይጮሃል" መሆን አለበት:: የአባባሉ ትርጓሜ እንዲህ ሲሆን "ከሐዲ ያጎረሰውን እጅ ይነክሳል"፤ "ዘይሴሰይ እክልየ አንሥአ ሰኮናሁ ላዕሌየ" (እንጀራዬን የበላ በኔ ላይ ተነሣብኝ) ለሚለው ተስማሚ ትርጉም ይሰጣል::

ውሾች ከሰው የበለጠ ጨዋዎች መሆናቸውን በራሳቸው ቃላት ሲነግሩን ከቅድስት ክርስቶስ ሠምራ ገድል ውስጥ ልንሰማ እንችላለን:: በሌላ አጋጣሚ እንደተናገርኩት፥ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ የኖሩት በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት (1375-1406) ነው:: በዚያ ጊዜ ጥቊር ሞት (Black Death, Bubonic Plague) የሚባል ተስቦ በዓለም ላይ ተዘርግቶ በሚሊዮን የሚቈጠር የዓለም ሕዝብ አልቋል፤ ከገድላቸው እንደምናነበው፥ እኛም ተቀሥፈናል:: የውሾቹ ታሪክ እንዲህ ነው፤ ሥጋ ሲጥሉላቸው፥ ሁሉም ተራቸው እስኪደርስ ይጠብቃሉ እንጂ አንዱ የሌላውን ለመውሰድ የሚሻማ አልነበረባቸውም:: በመገረም ቢጠየቁ የሰጡት መልስ፥ "እኛ እንደሰው ልጅ ስግብግቦች አይደለንም" የሚል ነበር::

በእኔ አስተያየት "ከባዳ ጉረስ፤ ወደወገንህ ተመለስ" ማለት ዝቅተኝነትን ማስተማር ነው::

ስደትና ፍልሰት የሚያስከትሉት ተጽእኖ በስደተኛው ላይ ብቻ ሳይሆን በአገሬው ሕዝብ ላይም ነው። ይኸም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች አሜሪካ ላይ ያደረጉት ተጽእኖ ገና ትልቅ ባይሆንም እየታየ መጥቷል። ለምሳሌ፥ ጤፍ አሜሪካ ይዘራል፤ የአበሻ ምግብ በየከተማው ይገኛል። አንዳንድ ምግብ ቤት እንግዶቹ ከኢትዮጵያውያን የአገሬው ሰዎች ይበልጣሉ። ሙዚቃችንም እየተሰማ ሄዷል።